# በዘንድሮው የቀድሞ ኢሕአፓ አባላት
# የራት ምሽት ላይ አረጋዊ በርሄን ማን ጋበዘው?

ከአቶሰውየው



ላለፉት 25 ዓመታት የሰሜን አሜሪካ የእግር ኳስ ዝግጅት በተደረጉባቸው ከተሞች ሁሉ፣ ዕድሉን አግኝተን የምንገኝ የቀድሞ የኢሕአፓ አባላት በወቅቱ የማንም ፓለቲካ ድርጅት አባል ሆንን አልሆንን ተገናኝተን ከሁላችን ልቡና ውስጥ የማይጠፉትን፤ ሕይወታቸውን ሰጥተው በኔ ዕምነት ሕይወት የሰጡንን ጓዶቻችንን የምናስታውስበት፤ በአንድ ምሽት ስለየግል ኑሮአችን፤ በእራት ግብዣው ሳይመጡ ስለቀሩትም ሆነ ያለፉ ጓዶቻችን እያነሳን የምንጨዋወትበት ወቅት ነው።

በትላንትናውም ምሽት በተገኙሁበት በዋሽንግተን ዲሲ በተደረገው የእራት ግብዣ፤ መገኘት ካላችሁት፤ ተገኝቼ እራትም ሳልበላ በንዴት ከውጭ ቆሜ አሳልፌ ወደመጣሁበት ተመልሼአለሁ። አዎን ዘንድሮ ዝግጅቱ እንደድሮው ሞቅ ያለ ሊሆን እንደማይችል አስቀድሜ ገምቼ ነበር። ምክንያቱም በኢሕአፓ ውስጥ አንጃኞች ከተፈጠሩ በኋላ (ላለፉት ስምንት ወራት) ዓይን ለዓይን መተያየት የማይችሉ ወገኖች እኔንም ጨምሮ ስለሚኖሩ ነበር። ነገር ግን ወደ እራቱ ሳመራ ዛሬ የፖለቲካ አቋማችን ምን ይሁን ምን ሁልጊዜም ይህ ዝግጅት ከእርስ በእርስ ግንኙነት አልፎ የሚያሳስቡን እኒያ በከተማና በገጠር፤ በዱር በገደሉ ወደ ኋላ ጥለናቸው የመጣናቸውን ጓዶቻችንን

ለማስታወስ ስለሆነ እንደወትሮውም ባይሆን ጥሩ ምሽት እናሳልፋለን ብዬ ነበር።

ግን ሁኔታው ለብዞዎቻችን ያልጠበቅነውና አሳዛኝ ሆኖ አግኝተነዋል። የተሰዉ ጓዶቻችንን ለማስታወስ በተዘጋጀው ዝግጅት ላይ ከቀልቤሳ ወይም ከግርማ ከበደ ባላነሰ ሁኔታ በንጹሐን ደም እጁ የተጨማለቀው ግለሰብ አቶ አረጋዊ በርሄ ፣ በጓዶቻችን ደም የታጠበ ከመካከላችን ይገኛል ብለን የጠበቅን አልነበርንም። ብዙዎቻችንንም በጣም አሳዝኖናል። አስቆጥቶናል። አረጋዊን ማን ጠራው? ያዘጋጁት ወገኖች እንዳልሆኑ ጠይቄ ተረድቻለሁ።

እዚህ ላይ በዋሺንግተን ዲሲ ያሉ ጓዶቻችን ይህንን ዝግጅት ለማቀናበር ብዙ እንደለፉበት ስለምረዳ ከፍተኛ ምስጋናዬን አቀርባለሁ። የዚህ ጽሑፌም ዓላማ እነዚህን ጓዶቼን ለመውቀስ እንዳልሆነ ይታወቅልኝ። አዎን ነገሩ በጣም ስላበሳጨኝ አረጋዊ በርሄ ወጥቶ እስኪሄድ ከውጭ የተቀመጥኩት የወያኔ ጦር የፈጫቸው ወኖቼን እርም አልበላም ብዬ ስለሆነና በዚህች ጽሑፍም የተሰማኝን ለመግለጽ ነው። ይህንንም ሰሜቴን በቦታው የነበሩ አብዛኞዎቹ ይጋሩታል። በሬ ካልሆንን በስተቀር ከአራጃችን ጋር አብረን አንበላም።

ሌላው የሚገርመው ነገር አረጋዊ በርሄ ገና ወደ አዳራሹ ሲገባ በቀጥታ የሄደውና ጅርባውን ሰጥቶን የተቀመጠው ከጋባዥቹ ከአንጃኞቹ መሪዎች ጌታቸው በጋሻውና መርሻ ዮሴፍ ከተቀመጡበት ጠረጴዛ ሲሆን ፤ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ግን ሁላችን እንድንመለከተው ይመስላል የወንበር ልውውጥ ተደርጎ ፊቱን በኩራት እንዲያሳየን ተደርጎአል። አንጃኞች በትላንትናው እለት ያሳዘናችሁት እኛን ብቻ ሳይሆን የወደቁትንም እንደሆነ ይግባችሁ። ግና ህሊና የለሾች ናችሁና ሀዘኔታን የምታውቁ አይመስለኝም።

አንድ አብሬ እሠራ የነበረ ከካናዳ የመጣ ጓድ ሊያጽናናኝ ሞክሮ፤ እባክህ ተዋቸው ኢሕአፓ እኮ ከአረጋዊ በርሄ ጋር በሕብረት ውሰጥ አብሮ ሠርቶ አልነበር እንዴ? አለኝ። አዎን አውቃለሁ ኢሕአፓ ለሀገር ብሎ ትላንት ካሳደዱት ሁሉ ጋር ለመሥራት ሞክሮአል። መታየት ያለበት ግን ይህ በየዓመቱ የሚደረግ የራት ግበዣ ሁላችንም በጋራ ከገዳዮቻችን ተለይተን የምንዘክራቸውን ጓዶቻችንን የምናስታውስበት ወቅት ስለሆነ ቢያንስ ከእነአረጋዊ በርሄ ዓይነቱ ገዳያቸው ጋር አብረን ማዕድ የምንቋረስበት በምንም ሊሆን አይገባም። ምናልባትም በነመርሻ፣ ጌታችውና እያግቸለቸሉ በሚነዱቸው የተሸራሞጠ ፓለቲከኞች ዕይታ፤ ለፓለቲካ ትርፍ ሲሉ የተሰዉትን ጓዶች ከማስታወስ ከነአረጋዊ ጋር ዳንኪራ መርገጥን መምረጣቸው ምን ያህል መዝቀታቸውን ያሳያል። አሁንም በድጋሚ አንጃው ከኢሕአፓነትና ከኢሕአፓ ታሪክ እራሱን እያገለለ የሚጓዙበትን መንገድ ግልጽ አድርጎ አሰይቶኛል።

ስለዚህም ለወደፊት የሚደረጉ ስብስቦች በማንኛውም ዓይነት ሁኔታ ከገዳዮቻችን ነጻ የሆነ መሆን ይኖርበታል ባይ ነኝ።

ጓዶች የዛሬውን ትተን የድሮውን በመመልከት አንነጋዳ ።

አመሰግናለሁ።

አቶሰውየው (ከሰሜን አሜሪካ)